በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

ነገረ ማርያም



አዘጋጅ ፡ ታይለማርያም ድረስ

መጋቢት 01/2017 ዓ.ም

መግቢያ

- በነገረ ድህነት ትምህርት ውስጥ "ምክንያተ ድህነት" የሆነችውን የአመቤታችንን ነገር ማወቅና መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።

  - ምክንያቱም እግዚአብሔር ተወለደ ሰው ሆነ ስንል እንዴት ሰው ሆነ የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ስለሆነ ነው።

የቀጠለ. . . .

- ከአዳም መርገም በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት ተጠብቃ የቆየች
- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የነገራትን ቃል በፍፁም እምነት ተቀብላ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ በማለትዋ እግዚአብሔር ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ፍፁም ሰው በመሆን እናት ትሆነው ዘንድ የመረጣት ፡
- ሰዎችን ለማዳን ባደረገው ጉዞ ውስጥ ሁሉ መከራን ተቀብላ ያገለገለች ስለሆነ ስለ እመቤታችን መማር ነገረ ድኅነትን ለመረዳት መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

የቀጠለ. . . .

- ነገረ ማርያም ትምህርት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሃይማኖት ደግማ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ክፍለ ትምህርት ነው።
- በመሆኑም ነገረ ማርያም ትምህርት የነገረ ድኅነት መሠረትና ምንጭ ነው።
- ቅድመ አለም በአምላክ ኅሊና ታስባ መኖሯን የድኅነት ተስፋ በተሰበከበት በዘመነ አበው በተለያየ ህብረ አምሳል መገለጧ ኋለም በዘመነ ነቢያት በተለያየ ኅብረ ትንቢት መነገሯን በዘመነ ሐዋርያትም በስብከታቸው ክብሯ መታወቁን በዘመነ ሊቃውንት በምስጢር ፣ በምስጋና በውዳሴ መዘከሯ መታወሷ በዚህ ክፍለ ትምህርት እንመለከታለን።

ምዕራፍ አንድ: የነገረ ማርያም ትምህርት መሠረታውያን (30 ደ)

1. የነገረ ማርያም ትምህርት መሠረታውያን

- ❖ *ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?*
- ❖ *ነገረ ማርያምን መማር ለምን አስፈለገ?*
- ❖ *የነገረ ማርያም ምንጮች*

ነገረ ማርያም/ትርጉም/:

- *ነገረ ማርያም* ከሁለት ቃላት የተገኘ /የተሰናሠለ/ ነው።
- *ነገር* ፡- የሚለው ቃል በቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ የአንድ ትምህርት መግለጫ አጉልቶ የሚያሳይ ሆኖ ያገለግላል።

የቀጠለ. . . .

- ***ማርያም*** **፡- ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የተሰጠ ክቡር ስም ነው።።**

ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?

- **ከሁለት ቃላት የተገኘ /የተሰናሰለ/ ሲሆን እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምሀሮ ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ንፅህና፣ ቅድስና፣ ዘለዓለማዊ ድንግልና ወ.ዘ.ተ የምንማርበት እንዲሁም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሰው ልጆች መዳን ውስጥ (በነገረ ድህነት) ያላትን ሱታፌ (አስተዋጽኦ) የምንረዳበት የትምህርት ክፍል ነው።**

የቀጠለ. . . .

ካገረ ማርያምን መማር ለምን አስፈለገ?

ሀ. ክርስትናን በአግባቡ ለመረዳት

- ክርስትና አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጦ የመሰረታት ናት።
- ቅድመ ዓለም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል ሆኖ ዓለምን የፈጠረ እና የሚገዛ እግዚአብሔር ቃል (ወልድ) ድሀረ ዓለም የጠፋውን አዳምን ፍለጋ በትሕትና እራሱን ዝቅ አድርጎ በሰው ባህርይ መገለጡን ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው መሆኑን የምናምንበት የምንረዳበት ትምህርት ነው።
- በዚህ በነገረ ድህነት የክርስትና ትምህርት ሰፊውን ድርሻ ይዛ የምትገኘው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።

ለ. ስለ እመቤታችን ፀጋ እና ክብር ለማወቅ

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአምላካችን ከልዑል እግዚአብሔር በተሰጣት ፀጋ ከነገደ መላእክት ከደቂቀ አዳም በክብር የሚመሰላት በፀጋ የሚተካከላት የለም።
- ይኸውም ከፍጡራን መካከል ተለይታ የአምላክ እናት ለመሆን የተመረጠች አምላክን በሀቱም ድንግልና ፀንሳ በሀቱም ድንግልና የወለደች፣ ሁሉን የሚመግበውን አምላክ ጡቶቿን አጥብታ ያሳደገች፣ በጀርባዋ ያዘለች፣ ስለ ልጇ የተሰደደች፣ በማስተማር ዘመኑ ከጌታችን ጋር የነበረች እስከ እግረ መስቀል ያልተለየች በመሆኗ ስለ እርሷ ስለተሰጣትም ፀጋ እና ክብር ለማወቅ አውቆም ለማክበር ነገረ ማርያም ትምህርት መማር ያስፈልጋል።

ሐ. በሕይወታችን ለመጠቀም

- በሕይወታችን ለመጠቀም፦ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣት የከበረ ቃል ኪዳን አለ።
- ቃልኪዳኑም *“ስምሽን የጠራ ዝክርሽን የዘከረ በቃል ኪዳንሽ የታመነውን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ አድነዋለሁ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እሰጠዋለሁ”* የሚል ነው።
- ይህ ቃል ኪዳን በህይወታችን እንዲሰራ በነፍስም በሥጋም ከኃጢአት በስተቀር የምንፈልገውና የሚገባን (የሚጠቅመን) ነገር እንዲፈፀምልን ይህንን የምናውቅበትን እና የምንረዳበትን ትምህርት ነገረ ማርያምን መማር ያስፈልጋል።

መ. ከቅዱሳን ጋር ባለህገሮችና ቤተሰቦች በመሆናችን (ኤፌ ፪÷፲፱)

- የቅዱሳን እናት ስለሆነችው ስለ እመቤታችን ማወቅ በክርስትና ስላገኘነዉ ሰማያዊ ቤተሰብ መረዳትና ማወቅ ነዉ።
  - “ከቅዱሳን ጋር ባለገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ።” ኤፌ ፪÷፲፱

የነገረ ማርያም ምንጮች

- የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጭ መሰረታቸው የሆነ መፅሐፍ ቅዱስ ነው። ይኸውም በሁለት የተከፈለ ነው ፡
  - ብሉይ ኪዳን እና ሐዲስ ኪዳን" በዚሁ በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን
  - የእመቤታችን ነገር በዘመነ ብሉይ በአበው ቀደምት ምሳሌ በነቢያት ትንቢት የተገለጠ
  - በዘመነ ሐዲስ በሐዋርያት ሰብከት ፍፃሜውን አግኝቶ የተሰበከ በመሆኑ ቅዱስ መፅሐፍ የነገረ ማርያም ምንጭ ነው።

የቀጠለ. . . .

- ከዚህ በተጨማሪ ለነገረ ማርያም ትምህርት ምንጭ የሚሆኑ
  - ተአምረ ማርያም፣
  - የቅዱስ ያሬድ ድርሰት፣
  - የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ማለትም
    - ✓አርጋኖን ዘእግዝእትነ ማርያም፣
    - ✓ሦስቱ ብርሃን፣
    - ✓እንዚራ ስብሐት፣
    - ✓መዓዛ ቅዳሴ
  - የአባ ሕርያቆስ ቅዳሴ
  - የቅዱስ ኤፍሬም ውዳሴ ወ.ዘ.ተ።

ማጠቃለያ

- የነገረ ማርያም ትምህርት መግቢያ የሚሆን ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ነገረ ማርያምን ትምህርት መማር ክርስትናን በአግባቡ ለመረዳት ስለ እመቤታችን ፀጋ እና ክብር ለማወቅ እንዲሁም በእመቤታችን ምልጃ በቅድስና ህይወቷ በህይወታችን ለመጠቀም ብሎም የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጮች መፅሐፍ ቅዱስና እና ሌሎች አዋልድ መፃህፍት መሆናቸውን እንረዳለን። በይበልጥ ደግሞ በነገረ ማርያም ዙሪያ የተፃፉ ነገሮችን ማንበብ ይረዳል።

በነገረ ማርያም ዙርያ የተጻፉ መጻሕፍት

- ሐውልተ ስምዕ/መምህር ኃይለማርያም ላቀው-2004ዓ.ም/
- ሕይወተ ማርያም ድንግል/ሊቀ ሊቃውንት ስምዓ ኮነ መላክ-2007ዓ.ም/
- ክብረ ድንግል/ሊቀ ሥልጣናት ሀብተማርያም ወርቅነህ (አባ መልከ ጼዴቅ) -1955ዓ.ም/
- ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ፩ እና ፪/መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ-በ2002 እና በ2004ዓ.ም/
- ታአዶኮስ/መምህር በጽሐ ዓለሙ-2010ዓ.ም/
- መድሎተ ጽድቅ ቅጽ ፩/ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ-2007 ዓ.ም-ክፍል ፪-ገጽ 266-325/
- አሐቲ ድንግል (በአባ ገብረ ኪዳን ግርማ)
- የብርሃን እናት በዲ/ን ሄኖክ ኃይሌ
- ወለዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት/በመጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ አንዱዓለም ዳግማዊ
- ነገረ ማርያም አዲሱ የግቢ ጉባኤ ኮርስ ማስተማሪያ/መምህር ሰሎሞን መኩሪያ/
- ነገረ ማርያም ነባሩ የግቢ ጉባኤ ኮርስ ማስተማሪያ/ሊቀ ጠበብት ሐረገወይን አገዘ/
- www.betedejene.com/ነገረ ማርያም፡- ከክፍል ፩-፳፬/

ይቅየን!

https://t.me/Hailemariamderese